# ያ ትውልድ

ቀን ፡ ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም. (July 19, 2021)

## “ዐባዬ ሞላልሽ! ሞላልሽ! ያሰብሽው ሆነልሽ”

*ከ«ያ ትውልድ ተቋም» የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ*

በቅድሚያ ለሙስሊሙ ኅብረተሰባችን ለዒድ አል-አድሐ ዐረፋ በዓል እንኳን አደረሳችሁ እንላለን።

የሁለተኛው ዙር የዐባይ ሙሌት በተሳካ ሁኔታ በመጠናቀቁ “ያ ትውልድ ተቋም” የተሰማንን ደስታ እንገልጻለን። ዐባይ ለኢትዮጵያችን ህልውና ለሕዝባችን ተስፋ መሆኑን እያሳየን ነው። ከጥንት ጀምሮ ሲያንገበግበን የነበረ የዐባይ ጉዳይ ዛሬ ዐባይ ፈሰሰ ሳይሆን ዐባይ ጠገበ፣ ዐባይ ሞላ ሲባል የጨለማ መገፈፍ ይታየናል። የዐባይ ሙሌት ለሀገራችን ብሔራዊ ክብር ኩራታችን ነው። ዐባይ ሲሞላ ሰንደቅ ዓላማችን ከፍ ይላል። ዐባይ ማደሪያ ሲያገኝ ሕዝባችን እፎይ ይላል። ለኢትዮጵያ መጮህ ማለትና የዐባይን ስኬት ማየት የማይነጣጠሉ ናቸው። “ዳቦ ለተራበ” ብለን ለተፈነከትንበት ዘለቄታዊ ምላሹ ዳቦ ማደል ሳይሆን ዐባይን ከፍ ማድረግ ነበርና በአንዳንዶች “የትም አይደርስ” የተባለው የህዳሴው ግድብ ስኬታማነት ያኮራናል።

ዐባይ ህይወት ነው። ይህን ግዙፍ የህዳሴ ግድብ ኢትዮጵያ እጅግ በአስቸጋሪና በተመሰቃቀለ ሁኔታ ውስጥ እያለች ከተራራው ጫፍ ማድረስ ሕዝባችን ከተባበረ፣ አንድነቱን ካጠነከረ፣ አጥሩን ከደረመሰ ከኢትዮጵያችን አልፎ ለአፍሪካ ኩራት እንደምንሆን አይጠረጠርም። የዐድዋ ድል የጥቁር ሕዝቦች ድል ሁኖ ቅኝ ተገዢዎችን ነጻ ሲያወጣ ወራሪዎችን አሳፍሯል፣ ቅሌት አከናንቧል። የዐባይ ስኬትም ከኢትዮጵያ አልፎ የአፍሪካ ኩራት ሁኖ ድህነት ላይ ዘምቶ፣ አንድነትን ወልዶ፣ ኢትዮጵያዊነትን አጠንክሮ እኛ ኢትዮጵያውያን ከተባበርንና ከሠራን ሥልጣኔን አብቃዮች ከመሆን የሚያግደን የለም። ዐባይን ለዚህ ካደረስን ያልተደረሰባቸው እምቅ የከርሰ ምድር ሀብቶቻችንስ? ማዕድናችን፣ ነዳጃችን ሁሉም በጃችን፤ ሁሉም በደጃችን መሆኑን ዐባይ ያስተምረናል። ድህነት ዐባይን ከገነባ፣ ዘረኝነት ሳይጠቀልለን ህዳሴን ከወለድን፣ ቋንቋ ሳይለያየን በአንድ ዐባይ ከፈካን ኢትዮጵያችን ብለን አንድ ህዝብ ከሆንን ኢትዮጵያ ላይ ዐባይን እንደገነባን ድህነትን፣ ድንቁርናን፣ በሽታን ጦርንርትን፣ መባላትን፣ ጥላቻን አሽቀንጥረን እንደምንጥል ዐባይ ይነግረናል።

ያ ትውልድ ለሀገሩና ለሕዝቡ ሲጮህ የኢትዮጵያን በጎ ተመኝቶ፣ እድገቷን ፈልጎ ነበርና ኢትዮጵያ ተፈጥሮዋን ዐባይ ልጇን ስታቅፍ፣ አቅፋ ብርሃን ልትረጭ ስትንደረደር ደስታችን ወደር የለውም። ጠላት ሳይቀር “ድሮም እነሱ” እንደምናሰኝ አንጠራጠር። ለጠላቶቻችንና ለሃያላኑ መንግሥታት ኢትዮጵያ የዐባይ ተጠቃሚ መሆን በታተናት ባሏት ሀገር ውስጥ ነገ የሚፈጥረውን ጉልበት፣ አንድነት፣ ፍቅር፣ አንድ ማእድ መጋራት፣መጎራረስ፣ መተቃቀፍ ሲታያቸው እየዘገነናቸው ቢሆንም ይቻሉት እንላለን። ዐባይ ብሄራዊ መለያችን ሰንደቃችን ነው። ዐባይ ከምድር አልፎ በአየር ሊምዘገዘግ ነው። ዐባይ በየቤታችን ሊጎበኘን ነው። እነሆ ዐባይ ከተተ! አለ። ጨለማ በዐባይ ሊዋጥ ነው፣ የእድገት ሞተሮች ዐባይ ቁልፍ ሊሆናቸው ነው። ዐባይ የዘረኝነት በትር ሊሆን ነው፣ “ከአክሱም ጫፍ” አቁማዳ እንዳለው ገጣሚ ከጣና ጫፍ ዐባይ መላዋን ኢትዮጵያን በብርሃን ሊዞር ነው። ዐባይ አቁማዳችንን ሊያስጥል ነው። “ዐባይ! ዐባይ! የሀገር ሲሳይ፤ አንድነትን አሳይ”፣ “ዐባዬ ሞላልሽ ሞላልሽ፤ ኢትዮጵያ ደስ ይበልሽ” ሊዘመርለት ነው። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ አላችሁ ደስ ብሎናል መልዕክታችን ከያ ትውልድ ወገኖች ይድረሳችሁ።

ዐባይ ለኢትዮጵያ!!!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!
ፈጣሪ ሀገራችንን እና ሕዝባችንን ይጠብቅ!!!
ያ ትውልድ ተቋም፡፡

Email : yatewlid@gmail.com
website : http://www.yatewlid.com, http://www.yatewlid.org
Facebook:- Yatewlid
ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም. (July 19, 2021)